በአስቸኳይ የሚወጣ፡- ነሐሴ 3 ቀን 2013 ዓ.ም.
*ለተጨማሪ መረጃ፡-*
**የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮ (LEOME) የኢትዮጲያ ተጠሪዎች**
ስቴፋኒ ሞንዶን smondon@iri.org
**በዋሺንግተን፣ ዲሲ የሚዲያ ተጠሪዎች**
ኦስቲን አከርስ aakers@iri.org +1-202-408-9450
ክሌይተን ማክሌስኪ media@ndi.org +1-202-728-5527

# የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI)/ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI) የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ የጋራ ውስን ተልዕኮ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገውን ብሔራዊ ምርጫ የተመለከተ ሪፖርት

ዋሺንግተን፣ ዲሲ – የኢትዮጵያን ምርጫ ከመታዘብ ውስን ተልዕኮ (LEOME) ጋር ተያይዞ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI) እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI) ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የተደረገውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ በተመለከተ የጋራ ሪፖርታቸውን ማውጣታቸውን ገለጹ። ሪፖርቱ (የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እና የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ድረገጾች ላይ ይገኛል) የምርጫ ምህዳሩን የተመለከተ መጠነ ሰፊ ትንታኔ የሚያቀርብ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ከሚያዝያ ወር ጀምሮ ከርቀት ሲያከናውን የቆየውን ትንተና እና በሀገር ውስጥ ያለውን ውስን የቴክኒክ ድጋፍ ግብዓት ያደረገ ነው። ኢትዮጵያ ሰኔ 14 ያደረገችው ምርጫ ወሳኝ ማሻሻያዎችን ተከትሎ የተደረገ ቢሆንም ሰፊ የጸጥታ ችግሮች፣ ግልጽ ግጭቶች እና በምርጫው ምህዳር ውስጥ ሌሎች ከባድ ውስንነቶች የነበሩ በመሆኑ የበረው ፖለቲካ ምህዳር፣ ተሳትፎ እና ፉክክር በከፍተኛ ሁኔታ የተገደበ ነበር።

የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ፕሬዝዳንት ዴሬክ ሚቼል እንዳሉት ከሆነ "ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም ከነበሩት ምርጫዎች ጋር ሲነጻጸር በተለይም ደግሞ ከብሔራዊው የምርጫ አካል እና በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በሲቪሉ ማህበረሰብ ከሚደረግ የምርጫ ክትትል ጋር በተያያዘ ወሳኝ መሻሻሎች የነበሩበት ቢሆንም ምህዳሩ ሲቪል ነጻነቶችን፣ እኩልነት የሰፈነባቸው የምርጫ ቅስቀሳ ሁኔታዎችን እና ጸጥታን የተመለከቱ አስፈላጊ ደረጃዎችን ያሟላ አልነበረም"።

የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት ፕሬዝዳንት ዳንኤል ትዋይኒንግ በበኩላቸው "ምንም እንኳን በምርጫው ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደሩ በርካታ ችግሮች የነበሩ ቢሆንም የኢትዮጵያ ህዝብ ቀጣዩ ጊዜ ጠንካራ በሆነ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የሚመሩበት እንዲሆን እንደሚፈልጉ በግልጽ ያሳዩበት ነበር" ብለዋል። በማከልም "ኢትዮጵያዊያን አሁን ብሔራዊ እርቅን ለማምጣት እና ተጨማሪ ዴሞክራሲያዊ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ተግተው መሥራት አለባቸው፤ ያለበለዚያ አሁን ያሉባቸው ተግዳሮቶች እንዳሉ ይቀጥላሉ" ብለዋል።

የተደረጉት ማሻሻያዎች ሲቪሉ ማህበረሰብ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው ሂደት ውስጥ ተዋንያን ሆነው ብቅ እንዲሉ ያስቻሉ መሆናቸውን በመጥቀስ ሪፖርቱ አወድሷል። በተጨማሪም የተደረጉት ማሻሻያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይበልጥ ነጻ እንዲሆን እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እና የዜጋ የምርጫ ክትትል እና የመራጮች ስልጠና የሚያከናውኑ ቡድኖችን ጨምሮ በኢትዮጵያ የሚገኙ ግለሰቦች እና ተቋማት አዎንታዊ ሥራዎችን እንዲሰሩ ያስቻሉ መሆናቸውን ሪፖርቱ ጠቅሷል። ሆኖም ግን ለረጅም ጊዜ የቆዩ የብሔር እና የቋንቋ እንዲሁም የፖለቲካ ኃይል ክፍፍሎችን መሰረት ያደረጉ በስፋት የሚስተዋሉ የጸጥታ ችግሮች እና ግልጽ ግጭቶች፣ በምርጫ የመጫወቻ ሜዳው ላይ ያለው የሚዛን መዛባት፣ የፖለቲካ ሀሳብን ከመግለጽ አንጻር ወደኋላ ሸርተት የማለት ሁኔታዎች መከሰታቸው፣ ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች እና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያስከተላቸው ውጤቶች የፖለቲካ ምህዳሩ፣ ተሳትፎው እና ፉክክሩ ውስን እንዲሆን እንዳደረጉ ተልዕኮው ገልጿል።

ትንተናው ከሚያዝያ 1 ጀምሮ እስከ ሐምሌ 8 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ተወካዮችን፣ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ ሚዲያውን፣ የዜጋ የምርጫ ታዛቢዎችን እና የዲፕሎማሲውን ማህበረሰብ ጨምሮ ከተለያዩ የምርጫ እና የፖለቲካ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ጥልቅ የበይነ መረብ ቃለ መጠይቆችን ግብዓት ያደረገ እንዲሁም ሁለቱም ኢንስቲትዩቶች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን ዕውቀት እና ግንኙነቶች መሠረት ያደረገ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የጤና ቀውስ በፈጠራቸው ውስንነቶች የተነሳ የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው የተከናወነው ከዓለም አቀፍ ምርጫ የመታዘብ መርሆዎች ዲክላሬሽን (Declaration of Principles for International Election Observation) እና ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር በሚጣጣም መልኩ ቀጣይነት ያለው ከርቀት

የሚከናወን ስልታዊ ትንተናን በመጠቀም ሲሆን በበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድን እና በምርጫው ቀን በቦታው በነበረ አነስተኛ የቴክኒክ ቡድን የተደገፈ ነበር። የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮው ከርቀት ሆኖ ሥራውን በሚያከናውን በአንጻሩ አነስ ያለ ቡድን አማካኝነት ጳጉሜ 1 የሚደረገውን ምርጫ በመገምገም በምርጫ 2013 ላይ የሚሠራውን የግምገማ ሥራ የሚቀጥል ይሆናል።

ይህ ሪፖርት ግንቦት 5 የወጣውን የበይነ መረብ የቅድመ-ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድን ሪፖርት (የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት እና የኢንተርናሽናል ሪፐብሎካን ኢንስቲትዩት ድረገጾች ላይ የሚገኝ) እና ሰኔ 2 የወጣውን የምርጫ ክትትል መግለጫ (የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት እና የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ድረገጾች ላይ የሚገኝ) መሠረት ያደረገ መጠነ ሰፊ ግምገማ ነው።

**ስለ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት**
ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI) የፖለቲካ ፓርቲዎች ይበልጥ ምላሽ ሰጪ እንዲሆኑ በማገዝ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለበት አስተዳደርን በማጠናከር እና ሴቶችን እና ወጣቶችን ጨምሮ የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በፖለቲካ ሂደት ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና በማሳደግ በዓለም ዙሪያ ነጻነትን እና ዴሞክራሲን የሚያራምድ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ የሆነ ድርጅት ነው። እ.ኤ.አ. ከ1983 ጀምሮ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት በዓለም አቀፍ የመታዘብ ተልዕኮዎች እና በግምገማዎች አማካኝነት በ60 ሀገራት ውስጥ ከ200 በላይ ምርጫዎችን ተከታትሏል። የሚከተለው ድረገጽ ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡- www.iri.org

**ስለ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት**
ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት የዴሞክራሲ ተቋማትን፣ ሂደቶችን፣ ልማዶችን እና እሴቶችን በማጠናከር እና በመጠበቅ ሁሉም ሰው የተሻለ ጥራት ያለው ህይወት እንደዲኖር ለማድረግ በዓለም ዙሪያ በአጋርነት የሚሠራ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ የሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ራዕዩ ዴሞክራሲ እና ነጻነት የሰፈነበት እና ሁሉም ሰው ሰብአዊ ክብሩ የተጠበቀበት ዓለም ተፈጥሮ ማየት ነው። ባለፉት 35 ዓመታት ውስጥ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ከ250 በላይ ምርጫ የመታዘብ ተልዕኮዎችን በ70 ሀገራት አከናውኗል። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.ndi.org

###